# ሠርግ

# በጥንታዊት ኢትዮጵያ እምነትና ባህል የሠርግ ሥነ ስርዓት

**ቀሲስ አስተርአየ ጽጌ**
nigatuasteraye@gmail.com

**ጥቅምት ፴ ቀን ፳፻፲ ዓ.ም.**

*ማሰሰቢያ፦ ይህች ጦማር ለሙሽሪት አክሊለ ብርሃን እና ለሙሽራው ድንቁ መንግሥቱ ጋብቻ በተዘጋጀው እራት ግብዣ፤ በከንሳስ ደብረሣኅል መድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን ቀርባ የነበረችውን ትምህርት የያዘች ናት። ወደ ጦማር ለመለወጥ ስዘጋጅ፤ ዓረቦች በወገኖቻችን ላይ የሚፈጽሙትን ግፍና በደል ሰማሁ፤ በአንድ ወቅት ባንድ ቤተሰብ ላይ ሞትና ሠርግ ባንድ ቀን ተፈጸሞ የደረሰባቸው ሁኔታ ተሰማኝ፤ ይህንንም በ፪ኛው አንቀጽ በ፰ኛው ገጽ ላይ ገልጨዋለሁ። ጦማሯ ሁሉንም ስለምትዳስስ ለሁሉም ቀርባ ሁሉም ቢያነባት ስለምትጠቅም ላንባቢ ትቅረብ የሚለው ሀሳብ ስለበዛ የቀረበች ናት።*

## <u>መግቢያ</u>

በጋብቻ የሚካሄደው ዝግጅት ለምን ሠርግ ተባለ ? የሚል ጥያቄ መነሣቱ ስለማይቀር ምክንያቱን እንደመግቢያ ልጠቀምበት አሰብኩ። ምክንያቱን ግልጽ ለማድረግ ሁለት ምሳሌዎችን በመጥቀስ እጀምራለሁ። ፩ኛ ወታደር ነው። ወታደራዊ ሠራዊት ድንበር አልፎ፤ ኬላ ጥሶ ወደ አንድ ሕብረተ ሰብ ሲገባ ሠርጎ ገባ ይባላል። ፪ኛው ደግሞ የወንዝ ጅረት ነው። አዋሽን የመሰለ ፈሳሽ ወንዝ ሄዶ የሚገባበት፤ የሚቆምበት እና የሚሰርግበት ቦታ ሠርግ ይባላል። የተጓዥ ሰብአዊ ቡድንና የፈሳሽ ወንዝ እንቅስቃሴና መዳረሻ የሚገለጽበት ሠርግ የተባለ ይህ ቃል ፤ ሁለት የተለያዩ ጾታዎች በተለያዩ ቤተሰቦች አድገው የጨዋታ ዘመናቸውን አቋርጠው ወደ ትዳር ሲገቡ፤ <u>የገቡበት ክንውን መነሻቸው፤ እንቅስቃሴያቸውና መድረሻቸው ሠርግ ተብሎ ተጠራበት።</u>

ሙሽራችን ድንቁ መንግሥቱ ወደ አክሊለ ብርሃን ሕይወትና ቤተሰብ ሠርጎ የገባበትን፤ ሙሽሪት አክሊለ ብርሃን ወደ ድንቁ መንግሥቱ ሕይወትና ቤተ ሰብ ሠርጋ የገባችበትን ክንውን (ሠርግ)፤ ከእኛ በፊት የነበሩ ኢትዮጵያውያን አባቶቻችን እና እናቶቻችን ሠርጋቸውን ባከናወኑበት፤ ኃጢአትና ነውር በሌለበት ባህላችን በዘፈን ለማከናወን በዚህ ቦታና ሰአት ተገኝተናል።

ሥርግ ለኦርቶዶክስ ተዋህዶ ክርስትና ነገረ መለኮት ማስረጃ ሆኖ እንደ ምሳሌ የቀረበ እና በባህላችን ውስጥ ተካተው ከተያዙት ኢትዮጵያዊነታችን አንዱ ነው።

- ፩ኛ፡-በነገረ መለኮት
- ፪ኛ፡-በይሁንታና በአሜንታ ሥርግን ማስተናገድ ተገቢ ነው።
- ፫ኛ፡-ኃጢአት ምንድነው?
- ፬ኛ፡-ኃጢአት ከልክ ማለፍ እና መጉደል ነው።
- ፭ኛ፡-በሥርግ ዘፍነን መዳር ወቅታዊ እና የተፈጥሮ ነጸብራቅ ነው።

በተዘረዘሩት አናቅጽ ስለ ሥርግ ከመምህራኖቼ የሰማሁትን፤ በነገረ መለኮቱ ያለውን ግንዛቤ በማስቀደም፤ ይህችን ጦማር እጀምራለሁ።

# ፩ኛ፡-<u>በነገረ መለኮት</u>

ፈጣሪ "ሰው ብቻውን ይሆን ዘንድ መልካም አይደለም የሚስማማውን ረዳት እንፍጠርለት ብሎ ሴትን ፈጠረ (ዘፍ ፪፥፲፰)።" የሚስማማውን ብሎ ፤ነገር ግን ለጾታው ተቃሪንውን ፈጠረ። የሚስማማውን ብሎ ለምን ተቃራኒ ወንድና ሴት አደረጋቸው የሚል ሀሳብ ሊመነጭ ይችላል። ወደ ሌላ ነገር ጎትቶ ከያዝነው ርእስ ስለሚያርቀን እዚህ ላይ ልግታውና ወደ ሥርጉ እንመለስ።

ክርስቶስ ከሰማይ ከወረደው መለኮቱ በቀር ድህነትን የፈጸመው በነበረው ምድራዊ ሰውነታችን፤ በምድራዊ ቋንቋ፤ በምንበላው ህብስት እና በምን ጠጣው ወይን ነው። የፈጸመውን ምሥጢረ ድህነት የክርስቲያና ድርጅት ከሚገልጹበት መንገድ በረቀቀ በጎላና እጅግ በሚያረካ መንገድ ስሜት፤ ከህዝባችን ሥነ ልቡና፤ ባህርይ፤ ታሪክ እና ሰብአዊ ክብራችን ጋራ በጠበቀ ሁኔታ በመዛመዱ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ነገረ መለኮት፤ CULTURAL & LIBERATION THEOLOGY ነው ተብሎ ይነገርለታል።

የቤተ ክርስቲያናችን የስነ መለኮት ጥናት LIBERATION THEOLOGY የተባለበት ምክንያት፤ ቤተ ክርስቲያናችን በዓለም ካሉት ሁሉ አብያተ ክርስቲያናት በተለየ መንገድ ያጠመቀቻቸውን የኢትዮጵያ ልጆች ፊደል ካስለየች በኋላ፤ የዳዊትን መጽሀፍ "ፍካሬ ዘጻድቃን ወዘ ኃጥአን" ብላ በውርድ ንባብ አፍ በማስፈታቷ ነው። በተጨማሪም፤ እመቤታችን አምላኳ ያደረገላትን በገለጠችበት ላይ "በልባቸው የሚታበዩትን በትኗቸዋል" (ሉቃስ ፩፥፶፩) ብላ የተናገረችውን፤ ቤተ ክርስቲያናችን በጸሎት መልክ አዘጋጅታ ለትንሹም ለትልቁም በቃሉ እንዲይዘው በማስተማሯ ነው። ከውጭ ሠርጎ የሚገባ፤ ሥርጎ ገብ ወራሪ፤ በተከሰተ ጊዜም የእመቤታችንን መግለጫ የነጻነት ወኔ መቀስቀሻ በማድረግ ህዝቡን ወደ ተዋጊ አርበኛነት በመለወጧ ነው።

CULTURAL THEOLOGY የተባለበትም ምክንያት እንደ ሥርግ የመሳሰሉትን ሁሉ ባህላውያን ነገሮች ከነገረ መለኮቱ ጋራ በማስተሳሰሯ ነው።

ለምሳሌ፦ “እንከሰኬ ኢኮኑ ክልኤ ዘእንበለ ፩ዱ ሥጋ እሙንቱ (ማቴ ፲፱፡፮)።” ማለትም፦ ሴትና ወንድ ከተጋቡ በኋላ አንድ አካል እንጅ ሁለት አይደሉም። ብሎ ክርስቶስ የተናገረለት ጋብቻ በባህላችን ሠርግ ተብሏል። ቅዱስ ጳውሎስ ክርስቶስ የተናገረውን መሠረት በማድረግ ስለ ሠርግ “ወይከውኑ ፪ሆሙ አሐደ ሥጋ ።ዐቢይ ውእቱ ዝነገር ወአንሰ እብሎ ላዕለ ክርስቶስ ወላእለ ቤተ ክርስቲያኑን (ኤፌ ፭፡፴፪)። ብሎ ተናግሯል። ይህም ማለት በሠርግ ወደ ጋብቻ የመጡ ሁለቱ ተቃራኒ ጾታዎች አንድ ሥጋ ይሆናሉ። ይህ የሠርግ ነገር ጥልቅ ረቂቅ ነገር ነው። እኔ ይህን ረቂቅ ምሥጢር በክርስቶስ እና በክርስቲያኖች መካከል ያለውን ጥልቅ ምስጢር እገነዝብበታለሁ።” ብሎ የተዋሕዶውን መሠረታዊ ግንዛቤ ለሠርግ ጥልቅ ምሥጢር እንደ ምሳሌ ጠቅሶታል።

እነ ቅዱስ ቄርሎስን የመሳሰሉ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ነገረ መለኮት ሊቃውንት “በኅብረተ ፪ቱ ህላውያት በተዋሕዶ ዘእንበለ ፍልጠት ወኢቱሳሔ ወኢውላጤ እስመ ሥጋ ውእቱ”(ቄርሎስ ፸፰፡፲፯) ማለትም፦ “በመለኮቱ እና በትስብእቱ ያለው የክርስቶስ ሥጋዊ እና መለኮታዊ ባሕርይ፤ አንዱን ያንዱ ባሕርይ እና ህልውና ሳይውጥ ሳያዛባ እኛን ለማዳን የተዋሀደበትን ለምሳሌ ጠቀሰው። ሊቃውንት አባቶቻችን በክርስቶስ ትምህርት ላይ የተመሠረተውን የሐዋርያትንና የነ ቅዱስ ቄርሎስን ጥልቅ የነገረ መለከትን ትምህርት በመከተል፤ የባልና ሚስትን ከሁለትነት ወደ አንድነት መምጣት፤ የክርስቶስን ባህርይ እና አካል ለ”ምስጢረ ከብካብ” (ሠርግ) መሠረት አድርገውታል። ኤራቅሊስ “ትዝምደ ዕጓለ እመሕያው በኩሉ ገጽ ወበብዙህ አምሳላት ”(፴፱፡፭)።” ማለትም፦ በብዙ አንጻር እና በብዙ ዘርፍ በመዛመድ መዳናችን ተከናወነ።” እያለ የተናገረውን በሙሽራው እና በሙሽሪት በኩሉ ያለውን ዘርፈ ብዙ ሐረግ መገናኘቱንና ወደ ዝምድና መምጣቱን ይገልጹበታል። እንደገና “ወአረቀ ትዝምደ ሰብእ ምስለ እግዚአብሔር ሊቀ ካህናቲሁ ለአብ (ሃይ ምዕ ፮፡፳፫)።” ይህም ማለት፦ክርስቶስ የአብ ሊቀ ካህናት ሆኖ ተራርቆ የነበረውን ሰውና እግዚአብሔርን አስታረቀ።” በባህላችንም ባንዳንድ ምክንያቶች ተራርቀው በጽብና በጠላትነት ይተያዩ የነበሩት ህብረተ ሰቦች፤ በጋብቻ ተሠራረገው ይቀራረባሉ። ይዛመዳሉ።

በበሰለው ቅኔያቸው ቅዱሳት መጻህፍትን የሚተረጉሙ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት “በኅብረተ ፪ቱ ህላውያት” የምትለዋን ሐረግ፤ አካላዊ ቃል ወደ ሰባዊ ባህርይ ሠርጎ በመግባት ያዳነበትን መንገድ፤ በሙሽራውና በሙሽሪት ውህደት የተከናወነውን ሠርግ ይመለከቱበታል።

አምላክ ፍቅር አስገድዶት በራሱ ስህተት የጠፋውን ሰው ፈልጎ ያድነው ዘንድ፤ በፈቃዱ የኛን ሰውነት ተዋሕዶ ያዳነበትን መንገድ ለመግለጽ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ “ነሥአ ለህላዌ ዚአነ ከመ ብእሲ ዘተኃጥአ ፍቅሩ; ወሮጸ ለሀሚሦቱ እስከ ረከቦ ወነሥአ ከመዝ ህላዌ ዚአነ ተኀጥአት እምእግዚአብሔር ወርህቀት እምኔሁ ጥቀ ወሮጸ ድህሬሃ እስከ ረከባ ወነሥኣ ወይእቲኒ ተወከፈቶ (ሃይ ፳፪፡፭)።” ብሎ ፍቅር በጠማው ጎልማሳ ምሳሌ ገለጸው። ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅን ንግግር፤ ኢትዮጵያውያን ሊቃውንት ከሠርግ ጽንሰ ሀሳብ ጋራ ያገናዝቡታል። ይህም ማለት፦ “የእኛን ሥጋና ነፍስ ተዋሕዶ ከአባቱ ከእግዚአብሔ ጋራ ያስታርቀን ዘንድ ያደረገውን ፍቅር፤ ፍቅረኛውን ያጣ ጎልማሳ ፍቅረኛውን እስኪያገኛት ድረስ ተግቶ እንደሚፈልግ እና ባገኛትም ጊዜ በፍቅሯ እንደሚረካ፤ እሷም በፍቅሯ እንደተቀበለችው” የሚገልጸውን ለተቀደሰው ሠርግ መሰረታዊ ምሳሌ ያደርጉታል።

ሁለት የተለያዩ ጾታዎች በተለያዩ ቤተሰቦች አድገው የጨዋታ ዘመናቸውን አቋርጠው ዘመዶቻቸውን ይዘው በሠርግ ወደ ትዳር ሲገቡ፤ የገቡበትን የሠርግ ክንውን፤ ሴቱ በዕልልታ ወንዱ በሆታ በስሜት በፍቅር በመግባባት ያከብሩታል። የሴቱ እልልታና የወንዱ ሆታ፡ ሠርጉን በይሁንታና በአሜንታ መቀበል ስለሆነ ኃጢአት አይደለም። አሜንታውንና ይሁንታውን ልግለጸው።

# ፩ኛ፦በይሁንታና በአሜንታ ሠርግን ማስተናገድ ተገቢ ነው።

ኢትዮጵያዊው የጋብቻ ሥርዓት በቤተ ክርስቲያናችን ከመከናወኑ በኋላም ሆነ በፊት፤ በወንድ እና በሴት ወገን ያሉ ሠርገኞች ከዓለም ለየት ባለ በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ በተመሠረተው መንገድ ይቀበሉታል። የሙሽራው ወገን፦

"የወይን አበበየ የወይን
የወይን አበበየ የወይን፤
እኛም ወደናል ትሁን" የሚለውን እየተቀባበሉ በመዝፈን፤ ከሌላ ቦታና ጎሳ ሠርጋ የገባቸውን ሙሽሪት፤በእልልታ ይቀበሏትል።

በሙሽሪት ወገን ያሉትም በበኩላቸው፦

"የወይን አበበየ የወይን
የወይን አበበየ የወይን፤
እኛም ወደናል ይሁን" የሚለውን እየተቀባበሉ በመዝፈን፤ ከሌላ ቦታና ጎሳ ሠርጎ የገባውን ሙሽራ በእልልታ እና በሆታ ይቀበሉታል።

በሠርግ ወቅት የሚከናወነው ኢትዮጵያዊ ዘፈንና እስክስታ (vibration) በተፈጥሮ እርግብግቦሽ (wave) ላይ የተመሰረተ እንቅስቃሴ ነው። የኢትዮጵያ የቅኔና የነገረ መለኮት መምህራን የተፈጥሮ እንቅስቃሴን ከሚያጠኑ ዘመናውያን ተመራማሪዎች ያለአነሰ ግንዛቤ አስጨብጠውናል።

አባቶቻችን፤ ኢትዮጵያውያን ጎሳዎች በሠርግ እና በሞት የሚፈጽሙትን ክንውን አብራርተው እንዳስተማሩን፤ ሠርግ እና ሞት እየተከናወነባቸው ከኛ የደረሱት ሥርዓቶች እግዚአብሔር የፈጠረውን ምሥጢርና ውበት እየተመለከትን የምናደንቅባቸው ናቸው።

የሁሉንም ጎሳዎች ባህል ለመዳሰስ በሰዓት በመወሰናችን በዚህ አጋጣሚ <u>በሠርግ ወቅት በተለያዩ ጎሳዎች ከሚቅርቡት አንዱን የጎጃምን ወስደን በጥሞና እንመልከት። የጎጃም እስክስታና ዘፈን አበባ በሚቀውት ንቦች እና በሚያዳቅሉት ቢራብሮዎች ክንፍ መርገብገብ ላይ የተመሰረተ ነው</u>።

ንቧ ማር ለመስራት ከሴቴ እና ከወንዴ እጸዋት ላይ አበባዎችን ለመቅሰውም ከምታደርገው መርገብገብ የተቀዳ ነው። ቢራቢሮዋም ዘር ለማዳቀል ከምታደርገው መርገብገብ የተገለበጠ ነው።

በሥርግ ጊዜ ኩታችን አደግድገን ጫፉና ጫፉን ይዘን እንደ ክንፍ በመዘርጋት የምናከናውነው እስክስታ በአበባዋ ሙሽሪትና በአበባው ሙሽራው መካከል የተሰራውን ፍቅር ለመመስከር ነው። ኩታው የመርገብገቢያውን ክንፍ ይወክላል። ኩታው የሚያሳየው ይህ ብቻ አይደለም። ቅዱሱ መጽሀፋችን እንደሚያዝዘን ዘጸ ፲፩፡ ፴፯_፵)፤ የፈጣሪን ትእዛዝ እንድናስብበት የተሰጠ ምልክት ስለሆነ ለሥርግ ብቻ ሳይሆን፤ ወገን በሞት በተለየን ጊዜ ዓለም በሟቹ የታጠፈች መሆኗን ለመመስከር የኩታውን ጫፍና ጫፍ አጋጥመንና ታጥቀን እየወዘወዝን በማልቀስ እንሸኝበታለን። በሥርግ ጊዜም አደግድገን ጫፍና ጫፉን ይዘን የምናከናውነው እስክስታ በኩታችን ጠርዝ ስንሞት የምንለብሰውን አፈር እየጋፍን፤

"ሞትና ኩነኔ ከኋላ ተመለስ፤
ሙሽሮቹ አብበው እስኪያፈሩ ድረስ።" የሚለውን በማንጎራጎር ነው።
እነዚህ ተፈጻሚዎች የተፈጥሮ ሕግጋት፤ መከናወን የሚገባቸው ስለሆኑ ማንም ሊሽራቸው ሊነቅፋቸውና ሊሰርዛቸው አይችልም።

በአንድ ወቅት በአንድ ቤተሰብ ላይ ሞትና ሥርግ ባንድ ቀን ተፈጸሞ እንዴት እንደተወጡት ሊቃውንት ሲናገሩ የሰማሁትን ልጥቀሰው። አበባውና እሸቱ የሚባሉ መንታ ልጆች ተወልደው አደጉ። ለአቀመ አዳም ሲደርሱ አንዱ ሊያገባ ለሥርጉ በመሞሸር ላይ ሳለ፤ አበባው የሚባለው መንትያውን እባብ ነድፎት ሙሽራው ተሞሽሮ ሊወጣ ሲል በዚያው ቀን ሞተ። ሥርግና ሞት፤ ዘፈንና ልቅሶ፤ ባንድ ቀን ተፈጸመ። በሥርጉ የሚከናወነውን ዘፈንና እስክስታ ይተው? ወይስ ለሞተው ሰው የሚደረገውን ልቅሶና ኀዘን ይተው? ይህን ፈታኝ ወቅት የሟችና የሙሽራው ወላጆች ሁለቱንም እንዴት እንዳከናወኑት እንመልከት።

እንደምናውቀው የጥንቱ ኢትዮጵያዊ ቤት በር አንድ ነው። ቤቱን ቀድደው ለሬሳው መውጫ በር አበጁለት። ለሞተው እና ለተሞሸረው እናትና አባት በቤቱ መካከል ወለልላይ ጀንዲ ተነጥፎላቸው ተቀመጡ፤ ታስቦ ክንውን የተጀመረለት ሙሽራ በነበረው በር እንዲወጣ፤ በድንገት የሞተው ልጅ ሬሳ በተቀደደው በር እንዲወጣ አደረጉ። እናትና አባት ከወለል ላይ በተነጠፈላቸው ጀንዲ ላይ ተቀምጠው፡-

ቀጣፊ ነው ተብሎ የሚታማው ሞት፡-
በጓሮ አልፎ ሲሄድ ሰዎቹ እያዩት፤
አበባውን አይቶ አልሄደም አልፎት
እኛንም አመሰን እሱንም ቀጠፎት
ሳያፈራ ቀረ፡ ወይም ሳያሽት" እያሉ ከተቀመጡበት ሳይንቀሳቀሱ ተገንዞ ወደ ቀብር በመወሰድ ላይ ወዳለው ፊታቸውን አዙረው ደረታቸውን እየደቁ በማንጎራጎር ሸኙት።
ተሞሽሮ በበሩ ወደሚወጣው ሙሽራ ልጃቸው ፊታቸውን አዙረው ከተቀመጡበት ሳይነሱ፡-

"ሞትና ኩነኔ ከመንገድ ተመለስ፤
አብበው አሽተው እስኪያፈሩ ድረስ።" የሚለውን እልል
እያሉ ሥርጋ የምትገባዋን ሙሽሪትን ያመጣ ዘንድ ሸኙት።" ይላሉ። በሞትና በሕወት ላይ ተመሥርቶ የሚከናወነውን ይህን ባህል ሊቃውንት አበው በእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ላይ በደረሰባት ሀዘንና ደስታ እንዴት እንዳስተናገደችው ይገልጹታል።

ቅድስት ድንግል እመቤታችን ክርስቶስ ሲወለድ የተፈጸመውን ትንግርት ሁሉ "በልቧ እያሰበች ትጠብቀው ነበር"(ሉቃ ፪፡፲፱) "የልጇ መከራና ሥቃይም አንጀቷን የሚቆርጥ ልቧን የሚሰነጥቅ "በነፍሷ የሚያልፍ ሰይፍ " (፪፡፴፭) ነበር። በሌላ በኩል ቅዱስ ገብርኤል "ተፈስሂ

ኦምልእተ ጸጋ እግዚአ ምስሌኪ ወቡርክት አንቲ እም አንስት"( ፩፡፳፰) ብሎ የነገራትን የደስታ ብሥራት እና፤ ቅድስት ኤሳቤጥም "ቡርክት አንቲ እምአንስት ወቡሩክ ፍሬ ከርስኪ፤ ፍሶበ ሰማእኩ ቃለኪ ትትአምኀኒ አንፈርአጸ እጓል በውስተ ከርስየ በፍስሀ ወበሐሴት"( ፩፡፵፪) ብላ የነገረቻትን የደስታ ቃል በልቧ ያዘች።

በነፍሷ የሚያልፈውን ሀዘንና ትካዜ ሳትተው፤ አምላኳ በለበሰው ሥጋ ለራሱ እናትነት ያበቃትን እያሰበች፤ አንጀት የሚቆርጠው ሰይፍ በሚያልፍበት ነፍሷ "ነፍሴ ሀሴት ታደርጋለች"( ፵፯) ብላ እልል አለች።

"መራዊሃ ለቤተ ክርስቲያን" ማለትም የቤተ ክርስቲያናችን ሙሽራ የተባለው ልጇ በሰራለት ትንግርት "ትውልድ ሁሉ ብጽእት ይሉኛል" በማለትም ዕልልታዋን ትውልድ ሁሉ ተካፋይ እንዲሆን ጋበዘች። ዛሬ እኛ የተዋህዶ ኦርቶዶክስ ክርስትና ተከታዮች በጸሎታችን "ብጽእት ነሽ" የምንለው ራሷ ላቀነቀነችው ተሰጥኦ ለመመለስ ነው። ተደራርቦ የመጣባትን ሀዘኑን በዋይታ ደስታውን በእልልታ አስተናገደች። በዚህ ግንዛቤ አባቶቻችን እና እናቶቻችን ቆራቢዎች መነኮሳት ሀዘናቸውን በዋይታ ደስታቸውን በዕልልታ እያስተናገዱ ከኛ አድርሰውታል።

ክርስቶስ ይህ ሥጋየ ነው ብሉት፤ ይህም ደሜ ነው ጠጡት ብሎ ከሚሰጠን ምሥጢርና ሥስርዓት ጋራ እንዳይጋጭ ለመጠንቀቅ በቃናው ሠርግ ላይ የተደረገውን ተአምር አስተውለን መረዳትም ይኖርብናል። በቃና ሠርግ ላይ የተዘጋጀው ወይን ያለቀበት ምክንያት አለው። በዓለም ላይ የሚደረገው ሁሉ ጊዜአዊ መሆኑን እያሳየ፤ በባህል የተዘጋጀው ወይን፤ "ለአዲስ ስርአት የሚሆን ለዘላለም የሆነ ደሜ ነው ጠጡት" ብሎ በወቅቱ ከሚያዘጋጀው ወይን ለመለየት ነው። ክርስቶስ ያዘጋጀልንን ወይን ለዘላለማዊ ህይወት ርካታ መሆኑን እንገነዘብበታለን። በዚህች ዓለም ስንኖር ወደ ዘላለም ህወት የማይሻገሩ "ምን አለበት አንድ ጊዜ በክርስቶስ ድነናል" እያልን አውቀን በድፍረት፤ ድንገት ሳናውቅ በስህተት የምናደርጋቸው ብዙ ነገሮች እያሉን፤ በሠርግ የሚደረገው ዘፍን እና ተለይቶና ጠፍቶ የኖረ ዘመድ ሲገናኝ፤ ፍሪዳ አርደን፤ ጠጅ ጥለን፦

"ጠላቶችህ ሁሉ ይቅር ብለው ነበር

እንኳን ደህና መጣህ ከሄድክበት አገር።" እያልን የምንቀበልበትን ዘፈን መንቀፍ ተገቢ አይደለም። ይህም ደግሞ በሉቃስ ወንጌል ም ፲፭፡ ቁ፳፫ ላይ ተጽፎ በምናነበው ላይ የተመሠረተ ነው።

ተራርቀው ይኖሩ የነበሩ ሙሽራውና ሙሽሪት ሲገናኙ፤ ዘመድ አዝማድ ጎረቤት ከግራ ከቀኝ እየተጠራራን የተፈጥሮን ሂደት በመብል በመጠጥ በታጀበ ደስታ ስሜታችንን እንገልጻለን። ሙሽሮች የገቡበት ሠርግ ክንውን ሴቱ በዕልልታ፤ ወንዱ በሆታ በስሜት በፍቅር በመግባባት በባህላችን እናከብረዋል። በመጨረሻም ለዘላለም ህይወት ይሆንላችሁ ዘንድ ጠጡ ብሎ የሰጠንን ሥጋውን በመብላት ደሙን በመጠጣት የሠርግን ዕልልታ እንደመድማለን። በሠርግ ወቅት የሴቱ ዕልልታና የወንዱ ሆታ ሠርጉን በይሁንታና በአሜንታ መቀበል ስለሆነ ኃጢአት ሊባል አይገባም። ይህ ምጽድቅን እንጅ ጽድቅን አያሳይም።

# ፫ኛ፦ኃጢአት ምንድነው?

"እስመ አበሳ ኃጢአት ይእቲ "(፩ ዮሐ ፫፡፬) በደል ኃጢአት ነው። የኃጢአት ትርጉም አመጽ ነው። ክርስቶስ "ወኩሉ ዘይገብራ ለኃጢአት ገብራ ውእቱ ለኃጢአት፡ ዮሐን ፰፡ ፴፬።" እንዳለው፦ ይህም ማለት፦ "ኃጢአት የሚያደርግ ሁሉ የኃጢአት ባሪያ ነው።" አመጸኛ መሆንም የኃጢአት ባሪያ መሆን ነው። በዚህ ግንዛቤ የኃጢአትን ዘርፍና ሐርግ አስፍተን ስንመለከት፤ ማንም ሰው በራሱ ላይ ሊደረግበት የማይፈልገውን በሌላ ሰው ላይ የሚያደርግ አመጸኛ (የኃጢአት በሪያ ) እንደሆነ እንረዳለን። ይህንንም የተናገረው ጌታችን ነው።

ኃጢአት የዲያብሎስ ባህርይ ነው። የዲያብሎስ ባህርያት የሀሰት ምንጭነት ነፍሰ ገዳይነት ነው። ሀሰት የሚናገር ነፍስ የሚገድል ሁሉ ራሱን የዲያብሎስ አገልጋይ ባሪያ ያደረገ ነው (ዮሐን ፰፡፵፫—፵፬))። ከመሞቱ በፊት ንስሀ ካልገባ ራሱን በዚህ ባህርይ የሚመራ ሁሉ፤ ክርስቶስ "ትመውቱ በኃጢአትክሙ" (ዮሐን ፰፡፳፩) እንዳለው በኃጢአት መርዝ እንደተበከለ ይሞታል።

ቅዱስ ጎርጎርዮስ "ንግበር ሠናየ በኀበ አብያጺነ ወፍቁራኒነ ወጸላእያኒነ ዘከመ ንፈቅድ ንህነ ይግበሩ ለነ (ጎር ፴፯፡፲፯) እንዳለው፤ ኃጢአት እግዚአብሄር እና ሰው የማይወደውን የራስን ህሊና ሰብሮ በህቡዕ እና በገሀድ ተገቢ ያልሆነ ለወገን ለአገር ጠላትንም አስተምሮ የማይመልስ ስራ መስራት ነው። የኃጢአትን ምንነትን ቅዱስ ያዕቆብ "መልካም የሆነውን ነገር ለማድረግ እንዳለበት እያወቀ የማያደርግ ሰው ኃጢአት ያደርጋል ( ምዕ ፬፡ ፲፯)።" ብሎ በተናገረው ለማጠቃለል፤ ኃጢአት ጋብቻ ማፍረስ፤ ህብረተ ሰብ ሲበተን፤ ዳር ድንበር ሲቃወስ፤ ቄስ ጳጳስ ሲዋሽ ሲቀጥፍ ሲዘሙት ሁሉም ከልኩ፤ ከመስፈርቱ፤ ከወሰኑ ሲያልፍ እያየን እኔ ምን አገባኝ ብለን ማለፍ ነው። "ኃጥዕ በደለኛ" መሆን ማለትም ጊዜውን ጠብቆ ሲፈነዳ ህብረተ ሰብ የሚጎዳ ብክለት ደብቆ ማያዝ ነው።

ከተወሰነው በላይ መብላት መጠጣት፤ መሳቅ ማልቀስ፤ መጨዋታ መተከዝ፤ ዋይታ ዘፈን ማብዛት ተገቢ አይደለም። ሁሉም ከወቅቱ፤ ከልኩ እና ከድንበሩ ካለፈ ከጥቅም ወደጉዳት ይዘልቃል። የምንመገበው የምንጠጣው ሁሉ ሰውነታችን ተጥቅሞ የጨረሰውን ለመተካት ነው። ከልክነት አልፎ በሰውነታችን ውስጥ ተርፎ የሚፈስ ከሆነ የሚከተለው ተውከት ነው። ከተውከት አምልጦ በሰውነታችን ከቀረ፤ ወደ ስባትና አሲድ ተለውጦ የሚገድል መርዝ ነው።

"ልክ" ማለት የስነ ልቡና ሚዛን ናት። "አቅምህን ልክህን እወቅ" የሚለው ኢትዮጵያዊው ምክርና ተግሳጽ የማይገሰስ ቀዋሚ ቅርስ ነው። <u>በሥርግ ላይ የሚደረገው እልልታና ሆታ ቦታውና ልኩ ስለሆነ ነውር ሊሆን አይችልም። ሥርግ ከክርስቶስ በቀር ቅድስት ድንግል እመቤታችንም ሳትቀር ፍጥረት ሁሉ በዚህች ምድር ወደ መኖር የሚመጣበት ብቸኛ መንገድ "ፈልፈለ ሕይት" የህይወት ምንጭ ነው።</u>

# ፬ኛ ኃጢአት ከልክ ማለፍ እና መጉደል ነው።

ክርስቶስ ስለ ጋብቻ ፍች በተጠየቀ ጊዜ "አንትሙሰ ተሀድጉ አንስቲአክሙ በከመ እከየ ልብክሙ ትካትሰ አኮ ከመዝ" ሲል በሰጠው መልስ፤ የባልና ሚስት መለያየት ከልብ ክፋት የፈለቀ ነው ብሎ ወደ ጥንት የተፈጥሮ ህግ (ሠርግ) መለሰው። ጋብቻን የሚከለክል ክስተት በልዩ ተአምር በሰውነት ላይ ካልተፈጠረ በቀር፤ ከሠርግ መራቅ ከስህተት ላይ መውደቅን ያስከትላል ማለት ነው።

በሠርግ ቅንብር ወደ ዚህ ዓለም የመጣው ሁሉ፤ አቅመ አዳም ላይ ሲደርስ በተገቢው ሰርግ መስመር ካልያዘ፤ የሰርጎ መግባት ባህርዩን በመሳት ከገዳም ወጥቶ ወደ ህብረተ ሰቡ ሠርጎ ይገባና፤ ከበረከት ይልቅ መርገምን ያስከትላል። አንድ ወንድ ካንዲት ሴት፤ አንዲት ሴት ካንድ ወንድ ከተለየች በልዩ ተአምር ጸጋ ካልተደገፈ(ች) በቀር በሚፈጠረው የህሊና ድንዛዜ፤ ጠባይ ወደ አጋናንንትነት ይለወጣል፤ ማስመሰልንና ማታለልን ውሸትንና ግብዝነትን ማፍለቅ ይጀምራል። ስለዚህ ነው ቅዱስ ጳውሎስ "እነዚህ ቀጣፊዎች የአጋንንትን ትምህርት እያስተማሩ መጋባትን የሚከለክሉ ሀሰተኞች ናቸው " (፩ ጢሞ ፬፡፪ —፫ ) ያለው። ይህ ባህርይ የተጠናወታቸው ሰዎች በመመጻደቅ ግርዶሽ ራሳቸውን ጠቅልለው፤ ሠርግንና እና በሰርግ ዙሪያ የሚከናወኑትን የቆየውን ሁሉ ባህል ይጸየፋሉ። "ከዝሙት ሽሹ ኃጢአት ሁሉ ከሥጋ ውጭ ነው። ዝሙትን የሚፈጽም ግን በገዛ አካሉ ላይ ኃጢአትን ይሠራል"( ፩ኛ ቆሮ ፮፡፲፰) ያለውን ሰርዘው ካንዲት ሴት ጋራ የሚታሰሩበትን ህጋዊ ሰንሰለት በጥሰው ከብዙ ሲቶች ጋራ የሚተሳሰሩበትን መረብ ይዘረጋሉ። ኃጢአት ይህ እንጅ ሠርግና በሰርግ ዙሪያ የሚከናወነው ባህላችን ኃጢአት አይደለም።

ዘፈንን ወደ ኃጢአት የሚቀይረው፤ የሥጋ ባህርይ ተብለው ከተዘረዘሩት ከመዳራት፤ ጣኦትን ከማምለክ፤ ከሟርት፤ ከጥላቻ፤ ከጠብ፤ ከቅናት፤ ከቁጣ፤ ራስን ከሌላው አብልጦ ከመውደድ፤ ከመለያየት፤ ከአድመኝነት፤ ከምቀኝነት እና ከስካር፤ እርስ በርስ በአሽሙር ከመጎነታትል እና ከከንቱ ውዳሴ ጋራ ታጅቦና ተቀላቅርሎ ሲቀርብ ነው (ገላ ፭፡፲፱— ፳፩)። በፍቅር በደስታ በሰላም በትእግስት በየዋህነት ራስን በመግዛት የሚደረገውን ሁሉ ክርስትና አይቃወምም።

ክርስትና የሚቃወመው ከመስፈርት ያለፈውን ሁሉ ነው። ለምሳሌ "ቀራጭ ወደ መንግሥተ ሰማይ አይገባም" የሚባለው ከወሰኑ ያለፈውን ቀራጭ ነው። ከወሰን ያለፈ ሁሉ የሚታየው ከወሰኑ እንዳለፈ ቀራጭ ነው። ከወሰኑ ያለፈውን ሁሉ "እንደ ቀራጭ ቆጥረህ ከቤተ ክርስቲያን ለየው" ይላል። ቀራጭ የተጠላው ከተገቢው በላይ ሰው በመግፈፉ እንጅ በልክ የሚደረገው ቀረጥ ኃጢአት አይደለም። ኃጢአት ቢሆን ኑሮ፤ ራሱ ጌታችን ክርስቶስ "የአሳውን አፍ ስትከፍት የምታገኘውን ዲናር በኔና ባንተ ስም ክፈል (ሉቃ ፲፯፡፳፯)።" ባላለም ነበር። ኃጢአት የሚሆነው ከተወሰነው በላይ ሲሄድ ው። ( ማቴ ፳፪፡፳፩)። የቀረጥ ስራ ሰውን የሚፈትን በመሆኑ ከወጥመዶች አንዱ ቢሆንም፤ "እውነት እላችኋለሁ ቀረጥ ሰብሳቢዎች ወደ እግዚአብሄር በመግባት ይቀድሟችኋል"( ማቴ ፳፩፡፴፩) እንደተባለው። ቅዱስ ብጹእ ነኝ፤ የበቃሁ ካህን ነኝ እያለን በመመጻደቅ ወደቤተ መቅደስ ከምንገባና ከምንወጣ ብዙዎቻችን ይልቅ በንጽህና በቅድስና የሚቀድሙን ቀራጮች ይኖራሉ።

ዘፈን ኃጢአት የሚሆነው መጠኑ ከሆነው ሠርግ አልፎ ለሌላ ነገር መገልገያ ሲሆን ነው። ቅዱስ ጳውሎስ እንዳለው፤ ያለ አንዳች ወቅታዊ ምክንያት ለዝሙት ለጣኦት ለመዳራት ለመጠጣት ከሚደረግ ነውር ጋራ ሲዳመር ብቻ ነው። <u>እንጅ በወቅቱ ማለትም እንደ ባህላችን</u>

በተፈጥሮ ላይ ተመስርቶ የሚደረገውን ዘፈን፣ ያለ ወቅቱ ለመዳራት ከሚደረገው ዘፈን ጋራ ደርቦ ለመምታት መሞከር ስህተት ነው።

# ፫ኛ፡-በሠርግ ዘፍነን መዳር ወቅታዊ እና የተፈጥሮ ነጸብራቅ ነው።

## ፫ኛሀ. የሠርግ ዘፈን ወቅታዊ ነው።

ቤተ ክርስቲያናችን በኦሪትና በነብያት ላይ የተመሰረተች ናት። "ለመዝፈን ለማልቀስ ጊዜ አለው"(መክ ፫፡፩—፱) እንዳለው አገር ሲፈርስ፣ የሰው ኑሮ ሲቃወስ፣ ሰው በሞት ሲለየን የማልቀስ ጊዜዎች እንደሆኑ፣ ሠርግም ለዘፈን ጊዜው ነው። ክርስትናውንም ታሪክንም ባህልንም ሳይገነዘቡ የሚነቅፉበትንና የሚያወግዙበትን ሳይረዱ፣ ተፈጥሮ በተለያዩ ወቅቶች የሚገልጣቸውን ለመቀበል ፈቃደኞች ያልሆኑትን "በገበያ የሚቀመጡ ልጆች ጓደኞቻቸውን እየጠሩ የዘፈን ዜማ አቀነቅንላችሁ አልተቀበላችሁም፣ የልቅሶ ዋይታ (ሙሾ) አቀነቅንላችሁ አልተቀበላችሁም፣ "(ማቴ ፲፩፡፲፯) ተብለው በክርስቶስ የተወቀሱትን ፈሪሳውያንን እንዳንመስል ልናስብ ይገባል።

አባቶች እንደነገሩን እንኳን ሰው ለወፎችም ዘፈን አላቸው። የኛ ዘፈንማ በወራሪ ባህል ሳይበከል ሳይቆራረጥ በቅብብሎሽ የመጣ ነው። <u>በሠርግ፣ በበዓላት እና በታላላቅ ወቅቶች የተዘፈኑት ዘፈኖች የተሸከሙት መልእክት የሚያንጸባርቁት፣ በተዘፈኑባቸው ወቅቶች በሕብረተ ሰባችን ላይ የተከናወኑትን ክስተቶች ነው።</u>

በመጽሐፍ መልክ ተጽፈው ቢቀርቡ፣ የምዕራቡ ዓለም እያደነቀ ለስነ ጽሁፍ እና HUMANITY (ሰው መሆንን) ጥናት ከሚያቀርበው ከሸክሥፔር መጽሐፍ ያላነስ ይዘት አለው። የጥበብ ቃና በሚል ርእስ ከታሸጉት ተብለው በአቶ ታማኝ በየነ እና ተወልደ በየነ የሚቀርቡት ኪነቶች፣ ወደፊቱ የሚመጣው ትውልድ ኢትዮጵያዊነትን ለማጥናት ቢፈልግ የሚረዱት ይሆናል ብየ እገምታለሁ።

ይህን የሚቃወሙ ሰዎች በባእድ ወራሪ መንፈስ በተበከለው እና በተቆራረሰው መንፈሳቸው የኢትዮጵያዊነትን ገጽ ስሜት እና እርዮት ወደሚፈልጉት ለመቀየር የሚደርጉትን ነጸብራቅ አጉልተው ማሳየታቸውን ከመረዳት በቀር፣ መንፈሳዊነትንና ክርስትናን አያሳይም።

አሁን ባለንበት ዘመን ነውር ባልሆነው ሁሉ ባህላችን ላይ በክርስትና ስም በየአቅጣጫው የሚደረግበት ወረራ፣ ከኢትዮጵያውያን ልጆች ልብም ላይ ለመንቀል የሚደረገው ዘመቻ፣ ቀላል አይደለም። መጀመሪያ ኢትዮጵያዊነትን የማያውቁ ወይም እያወቁ በክርስትና ስም የመጡ ሰዎች አጣመው ያቀረቡላቸውን በመቀበል ኢትዮጵያዊውን ባህል የሰይጣን ነው ብለው እንዲሸሹት አደረጉ። በባእዳን ሰባኪዎች የተሰበኩ ወገኖቻችን ከራሳቸው ባህል መሸሽ ብቻ አይደለም፣ ክርስትናን ከውጭ ካመጡት እንደወረደ ተቀብለው ከላይ ሲወርድ በመጣው ነውር በሌለበት ባህል ላይ ዘመቱበት።

የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ልጆች ነን የምንል ሁሉ ልናስብበትም የሚገባን፤ ባለፉት ፳ አመታት የተነሳው ትውልድ በኛው ቤተ ክርስቲያን ጉያ እያሉ ቤተ ክርስቲያናችን ቀምራ የሰጠችንን ነገረ መለኮትና ባህል ላይ ስለሚያደርጉት ዘመቻ ነው። ሁሉም ጽድቅ መስሎ የታያቸውን የየራሳቸውን ጽድቅ ለመትከል የበረውን ቅዱስ ባህላችንን እየነቃቀሉት ነው።

ቅዱስ ጳውሎስ የተቃወመው፤ ከዝሙት፤፤ ከርኩሰት፤ ከመዳራት፤ ከጣኦት፤ ከሟርት፤ ከቅናትና ከስካር የተቀላቀለውን ዘፍን እንጅ፤ የተፈጥሮ ነጸብራቅ የሆኑትን በኢትዮጵያዊነት ግንዛቤ በየወቅቱ እየተቀመሩ የኖሩትን በሠርግ ጊዜ እና በተለያዩ ወቅቶች የተዘጋጁትን የዘፈን ዓይነቶች አይደለም።

# ፮ኛ ለ.የሠርግ ዘፈን የተፈጥሮ ነጸብራቅ ነው።

በኢትዮጵያዊው ቅኔ ተፈጥሮን ተገንዝበው ወደ ነገረ መለኮቱ ትርጓሜ የተሻገሩት ኢትዮጵያውያን ሊቃውንት እንደነገሩን፤ በምድረ ኢትዮጵያ ያሉ ሁሉ ጎሳዎች በየባህላቸው የሚያደርጉት ዘፈንና ልቅሶ ደስታና ሀዘን በስነ ፍጥረት ላይ የተመሰረቱ የተፈጥሮ ነጸብራቆች ናቸው። “አንዳንድ ጊዜ በዋልባም ይዘፈናል”የሚባለው በዚሁ ምክንያት ነው።

እኛ ዛሬ በዚህ ቦታና ወቅት ካንዲት ኢትዮጵያ እናት አገራችን ማህጸን የፈለቅን ብንሆንም፤ ከተለያዩ ወረዳዎችና መንደሮች የመጣን ከአገራችን ርቀን የምንኖር ነን። የሙሽራውና የሙሽሪት ቤተ ሰቦች፤ ዳሪዎች፤ የሠርግ ሚዜዎች በመሆን ሀላፊነቱን ተሸክመናል። ሙሽራውና ሙሽሪት እርስ በርሳቸው ተሰራርገው አንዱ በሌላው ህይወት ሲገቡ፤ ለሁሉም አባት እናት ወዳጅ ዘመድ ሆነን የምንዛመደው የምንሰራረገው እኛው ነን።

“ሞትና ከነኔ ከመንገድ ተመለስ፤
አብበው አሽተው እስኪያፈሩ ድረስ።” እያልን ለሁሉም የንምዘፈነው እኛው ነን። የሙሽራው ወገን በመሆን፦
“የወይን አበበየ የወይን
እኛም ወደናል ትሁን” ብለን ሙሽራው የመረጣትን ሙሽሪት የምንቀበላት እኛው ነን። የሙሽሪት ወገን በመሆንም፦
“የወይን አበበየ የወይን

እኛም ወደናል ይሁን”

ብለን ሙሽሪት የመረጠችውን ሙሽራ የምንቀበለው እኛው ነን። የተፈጥሮ ነጸብራቅ በሆነው ኢትዮጵያዊው ባህላችን የሙሽሮቻችንን የአክሊለ ብርሃንን እና የድንቁ መንግሥቱን ሠርግ በዚህ ወቅት እንድንቀበል የፈቀደልን አምላክ የተመሰገነ ይሁን! ሠርጋቸውን (ጋብቻቸውን) እግዚአብሔር ይባርክልን።

ከዚህ ቀደም የተጻፉትን ጦማሮች ለማንበብ ከፈለጉ የሚከተለውን ድረ ገጽ ይመልከቱ።

http://www.medhanialemeotcks.org/